በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/ 203210

ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ገመቹ ቤኩማ፡- ጠበቅ ፍቅሬ ሞያ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ሔና ፋርም ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ አመልካች ያቀረበዉ ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ ማስፈቀጃ ጥያቄ ተቀባይነት ባለማግኘቱ የቀረበ አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ በተጠሪ ሆቴል ውስጥ ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ ያለጥፋት የስራ ውል ስለአቋረጠብኝ የስራ ስንብት ክፍያዎች እንዲከፈለኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አመልካችን አላሰናበትንም ይልቁንም አመልካች ካለበት ዕዳ ለመሸሽ ሲል ስራውን ለቆ በመሄዱ ተጠሪ ላይ ጉዳት ደርሷል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የስራ ውሉ በአሰሪዉ ስለመቋረጡ ያላስረዳ በመሆኑ ተጠሪ የስራ ውሉ ያላግባብ አቋርጧል ለማለት አልተቻለም በማለት የክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ያልተከፈል ደመወዝ እና የዓመት እረፍት እንዲከፈለው ሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ያቀረበዉ ይግባኝ ጊዜ አልፎበታል ስለተባለ የይግባኝ ጊዜ ያለፈበት ምክንያት በመግለጽ መስከረም 08 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኙን በወቅቱ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ያልቻለው የአመልካች ጠበቃ አጋጠመኝ ባሉት እክል ምክንያት በፍቃድ መጠየቂያው ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ምክንያት ይግባኙን በጊዜው ለማቅረብ ያልቻለው በአመልካች ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ወይም በወኪሉ ያለመቅረብና በነዚሁ ጉድለት መሆኑ የታወቀ እንደሆነ ምክንያቱ እንደበቂ ምክንያት እንደማይወሰድ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 326(2) በህጉ የተመለከተ በመሆኑ ይግባኙ በጊዜ ያልቀረበው በበቂ ምክንያት አይደለም በማለት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ በሕግ የተፈቀደው የ30 ቀን ጊዜው ሳያልፍ በ26/12/2012 ዓ.ም ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሬጅስትራር የይግባኝ አቤቱታዬን አቅርቤ የስር መዝገብ ግልባጭ እንዲላክ በማህተም አድርጎ ለሥር ፍ/ቤት ተመርቶ፣በዚሁ መሰረት ለስር ፍ/ቤት አቅርቤ በዚሁ ቀን በ26/12/2012 ዓ.ም የመዝገብ ግልባጭ ተሰጥቶኝ በቦርሳዬ አድርጌ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለማቅረብ ዝግጅት ላይ እያለሁ ከቦርሳዬ ጋር ጠፍቷል፡፡በመሆኑም የይግባኝ አቤቱታዬን አቅርቤ የይግባኝ ፋይል ቁጥር አሰጥቼ የይርጋ ጊዜ አቋርጫለሁ፣በጊዜ ማቅረብ ያልቻኩት የመዝገብ ግልባጩን ነው፣ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት የይግባኝ ጊዜው ሳያልፍ ጊዜው አልፏል፣በቂ ምክንያት አልቀረበም በማለት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ ይግባኙን ለማቅረብ እንዲፈቀድልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ዋና ፍርድ የተሰጠው ሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ አቤቱታ ያቀረበው ደግሞ ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ከመሆኑ አኳያ በወቅቱ ይግባኙ አልቀረበም ሊባል የሚችልበት አግባብ አለው ወይ የሚለው ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ተጠሪ መጥሪያ ድርሶት መልስ ባለማቅረቡ የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንደመረመርነዉ ክሱ የስራ ዉል መቋረጥ በመቃወም የቀረበ የግል የሥራ ክርክር ሲሆን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ይግባኙ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚገባዉ በሰላሳ ቀን ዉስጥ መሆን እንዳለበት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139/3/ይደነግጋል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠዉ በሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን ይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ያቀረበው ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ነገር ግን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የቀረበዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልበጭ እና የይግባኝ ቅሬታ ብቻ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ እንዲቀርብ በሬጅስትራር ጽ/ቤት በመታዘዙ ይህ ተሟልቶ እስኪቀርብ በዚህ ሂደት ጊዜ ያለፈበት ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡ከዚህ እንደምንገነዘበዉ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉንና የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ይግባኝ ማቅረቢያ በህጉ የተመለከተዉ ሰላሳ ቀን ሳያልፍ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማቅረቡን ያሣያል፡፡ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ተያይዞ ባለመቅረቡ መዝገቡ ተከፍቶ ለችሎት ሳይቀርብ ጊዜዉ እንዳለፈበት አከራካሪ ባይሆንም የአመልካች ጉድለት ነዉ ተብሎ መወሰዱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ማየት አስፈላጊ ነዉ፡፡

የፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ስለይግባኝ ማመልካቻ ይዘትና አቀራረብ የሚደነግግዉ ክፍል ላይ እንደተመለከተዉ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠዉ ፍርድ ቤት የመዝገብና የፍርድ ግልባጭ ትክክል ግልባጭ ለመሆኑ ታትሞበትና ተፈርሞበት ከይግባኙ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ ለይግባኝ ሰሚ ቤት መቅረብ እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 327/2/ ላይ ተደንግጓል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ ወገን ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈለግ ለፍርድ ቤቱ አሳዉቆ የይግባኝ ቅሬታዉን አዘጋጅቶ ካቀረበ የፍርዱን እና የመዝገቡን ትክክለኛ ግልባጭ አሟልቶ መስጠት የፍርድ ቤቱ ሃላፊነት መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ በፍርድ ቤት ያለዉ አሁናዊ አሰራር ሲታይ የመዝገብ ግልባጭ ወይም መዝገቡ ለይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚቀርበዉ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ሲጠየቅ ወይም በችሎት ሲታዘዝ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህ አሰራር በአንድ በኩል ከህጉ ጋር የሚጣጣም አለመሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ በፍርድ ቤቶች ካለዉ የሥራ ጫና አኳያ የመዝገብ ግልባጭ እስከሚዘጋጅ የይግባኝ ጊዜ እንዳያልፍበት ታስቦ የተዘረጋ አሰራር ከመሆኑ አንጻር ሲታይ በዚህ ሂደት የሚፈጀዉ ጊዜ በተከራካሪ ወገን ጉድለት ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ጉዳዩም በዋናነት መታየት የሚገባዉ የይግባኝ መብት በማያጣብብ ሁኔታ መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡ይሁንና የመዝገቡ ግልባጭ ተሟልቶ ለባለጉዳዩ ከተሰጠ ሳይዘገይ ለይግባኝ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰሚዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ አመልካች የይግባኝ ቅሬታዉንና የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ የይግባኝ ማቅረቢያ ሰላሳ ቀን ሳያልፍበት ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ማቅረቡ አከራካሪ አይደለም፡፡ነገር ግን የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ ለመጠባበቅ ተብሎ በዚህ ሂደት ጊዜ ያለፈበት በመሆኑ ለዚህ ዋነኛ ምክንያት የአመልካች ጠበቃ ወይም የባለጉዳዩ ጉድለት ነዉ ሊባል አይገባም፡፡በሌላ በኩል በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት ትእዛዝ መሰረት የሥር መዝገብ ግልበጭ ለአመልካች ጠበቃ ከተሰጠ በኋላ ይህ ሰነድ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ እንደጠፋባቸዉ የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡትን ምክንያት ተገቢነትና አሳማኝነት ሳይመረምር የጠበቃዉ ጉድለት ነዉ የሚለዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊከሰት የሚችል እዉነታን ያላገናዘበ በመሆኑ ተገቢ ምክንያት ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የይግባኝ ጊዜ ሳያልፍ የይግባኝ ቅሬታ እና የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት አቅርበዉ እያለ በፍርድ ቤቱ አሰራር ምክንያት የስር መዝገብ ግልባጭ ተያይዞ ባለመቅረቡ ለተፈጠረዉ መዘግየት ምክንያቱ የአመልካች ወይም የጠበቃዉ ቸልተኝነትና ጉድለት ነዉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ህጉን እና በፍርድ ቤቱ ያለዉ አሰራር ያስከተለዉን ሁኔታ ያላገናዘበ ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/256736 ላይ በ09/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/ ይህ ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ አስር የስራ ቀን ዉስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ብለናል፡፡ይጻፍ

**መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም